የንግድና ቀጠናዊ ትስስር የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ግንቦት / 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ፡ መግቢያ 2
1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study) 2
1.2. የዘርፉ አጠቃላይ ነባራዊ ገፅታ 3
1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study) 4
1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡- 4
1.3.2. ንዑስ አላማዎች፡- 4
1.4. የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ምንነትና ጠቀሜታው 4
ክፍል ሁለት፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የሙስና ስጋት የተዛማጅ ጹሁፎች ዳሰሳ 5
2.1. በዘርፉ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ 5
2.2. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች 7
ክፍል ሦስት፡ የዘርፉ የጥናት ሰነ ዘዴ 8
3.1. የጥናቱ ቦታ እና ወሰን 8
3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች 8
3.3. ጥናቱ የተከናወነበት ሂደት 9
3.4. የሙስና ስጋት ጥናት ስነ-ዘዴ 9
3.5. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ 10
3.6. የጥናቱ ተግዳሮቶች 10
ክፍል አራት፡ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና 10
4.1. ተቋማዊ አደረጃጀት 10
4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን 12
4.3. የተቋማት ግልጽነት 13
4.4. አዋጅ፣ ድንብና መመሪያ 15
4.5. የንብረት አስተዳደር 16
4.6. የግዥ አስተዳደር 17
4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር 17
4.8 የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ 18
4.9. የፕሮጀክት አስተዳደር 19
4.10. ኦዲትና ቁጥጥር 19
4.11. የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና 20
ክፍል አምስት፡ የመፍትሄ ሀሳቦች 20
ማጣቀሻ ጽሁፎች 22

አባሪ ሀ፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስ ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና..23

ክፍል አንድ፡ መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጎዱ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው። ሙስና ማለት ባለስልጣኖች/ሀላፊዎች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል መበልጸጊያ የማዋል ብልሹ አሰራር ማለት ነው። ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው። ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል። የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል እና ህገ-መንግስታዊ ተቋማትን እና ስልጣንን አለማክበር የሙስና መገለጫዎች ናቸዉ።

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል። ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል። እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል። ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው። በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል።

በዚሁ መሰረት በተያዘው በጀት አመት ዘርፍ ተኮር አሰራርን በመከተል በ19 ዘርፎች ስር የሚገኙ ተቋማት የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን ስጋቶችን በመለየት እና የመፍትሄ ሀሳቦችን መስጠት የሚያስችል ጥናት አካሄዷል።

በተቋማት ለሙስና ስጋት እንደመነሻ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ሁኔታዎች ማለትም የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች

የሥነምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ለተለያዩ የሙስና አይነት መከሰት መንስኤዎች ናቸው።

በመሆኑም ይህ የጥናት ሪፖርት በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ በሚገኙ ሰባት ተቋማት በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በ11 ርዕሰ ጉዳዮች መሰረት ለተለዩ የሙስና ስጋቶች የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማመላከት ተሞክሯል።

1.2. የዘርፉ አጠቃላይ ነባራዊ ገፅታ

ለአንድ ሀገር እድገት አስተዋፅዖ ከሚያደርጉ ዘርፎች መካከል አንዱ የንግድ ዘርፍ ነው። ይህ የንግድ ዘርፍ በሀገሪቷ እድገት ላይ የሚያመጣው ጥቅም ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ህገ-ወጥ የንግድ ስራ ስር እየሰደደ መምጣቱ በሀገሪቷ ላይም ሆነ በህጋዊ መንገድ በሚሰሩት ነጋዴዎች ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ። በኮንትሮባንድ ምክንያት የሚመጣው ይህ ህገ-ወጥ የንግድ ስራ በሀገሪቱ በተለያዩ ከተሞች እያስከተለ ያለው ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ አስጊ እንደሆነ ነባራዊ ሁኔታዎች ያሳያሉ። በዚህ ህገ-ወጥ የአልባሳት ንግድ ስራ ላይ የሚሰማሩ ነጋዴዎች በርካሽ ዋጋ ከኮንትሮባንድ ነጋዴዎች የሚያገኙትን የተለያዩ አልባሳት ለተጠቃሚዎች በህጋዊ መንገድ ከሚሰሩ ነጋዴዎች በእጥፍ በሚያንስ ዋጋ በመሸጥ በህጋዊ መንገድ በሚሰሩ ነጋዴዎች ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ እና ሀገሪቷ ማግኘት እያለባት ባላገኘችው ገቢ ማሟላት እያለባት ያላሟለችው የመሰረት ልማቶች በእነዚ ህገ-ወጥ ነጋዴዎች ምክንያት ብዙ ነው። የንግድ ቦታ ማጣት በእነዚህ ህገ-ወጥ ነጋዴዎች እንደ ዋንኛ ምክንያት ቢነሳም ሀገሪቷ ባመቻቸችው የንግድ ስርዐት መሰረት ማንኛውም ዜጋ የንግድ ቦታ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው። ነገርግን እነዚህ ነጋዴዎች የሚያገኙት ገቢ በህጋዊ ከሚሰሩት አንፃር ከፍተኛ ስለሆነ በዚህ ህገ-ወጥ የንግድ ሰራ ላይ መሰማራት አዋጭ እንደሆነ በህገ-ወጥ መንገድ የተሰማሩት ነጋዴዎች ብዛት ምስክር ነው። ይህ ህገ-ወጥ የንግድ ስራ እየቀጠለ ከመጣ የሀገራችን መፃኢ ዕድል ከፍተኛ ችግር ውሰጥ ይወድቃል።

በኢትዮጵያ ምርቶችን በብቸኝነት የሚያመጡ አካላት ዋጋን እንደፈለጉ የመተመን ችግር ይታየባቸዋል። እንዲሁም ምርቶችን በመደበቅ እጥረት ፈጥሮ ዋጋን ባልተገባ መንገድ ለማናር የሚፈፀሙ ድብቅ ተግባራት እንደሚፈፀሙም የንግዱ ማህበረሰብ ጭምር የሚታዘቧቸው እውነታዎች ናቸው። በሌላ በኩል የሀገሪቱን ሰላምና መረጋጋት በማስፈን የንግድ እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን ማነቃቃት ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባው ተግባር ነው። በአሁኑ ስዓት በሀገሪቱ ለኑሮ ውድነቱ መባባስ እንደ ትልቅ ተግዳሮት ከሚጠቀሱት መካከል አንዱ በግብይት ሂደቱ ውስጥ የሕገወጥ ደላሎች ጣልቃ ገብነት ነው። ዘርፉ በርካታ ተግዳሮቶች የሚታዩበት ሲሆን ከእነዚህ መካከል የንግዱ ማህበረሰብ የስነ-ምግባር

ጉድለት፣ የንግዱ ማህበረሰብ የገቢያ አሻጥር፣ የአስመጭና ሊኪዎች የግብይት ጥሰቶች፣ የገቢ ዕቃዎች የጥራት ቁጥጥር ማነስ፣ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ክፍተቶች፣ የነዳጅ አቅርቦበትና ስርጭት ውስንነቶች፣ የዕቃ ደረጃ አሰጣጥ ችግር፣ የቁጥጥር አካላት ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣት በዘርፉ ከሚታዩ ችግሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ በውስጡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርን ጨምሮ ሰባት ተቋማት ያለው ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263 /2014 የተቋቋሙ ተቋማት የያዘ ዘርፍ ሲሆን ተቋማቱ በህግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በሀገር ደረጃ የንግድ አሰራርን በማዘመን፤ ግልፅ፤ ተደራሽና ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ ቀጠናዊ ትስስርን በማጠናከር፤ የውጭ ንግድን በማስፋፋትና በማሳደግ፤ የዕቃዎችን የጥራት ደረጃ በማዘጋጀትና በመቆጣጠር የሸማቹን፤ የንግዱን ማህበረሰብ እና የሀገርን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ተልእኮ የማሳካት ሓላፊነት ያለበት ዘርፍ ሲሆን ይህን ዘርፍ ጠንካራ ሆኖ እንዲወጣ ከፀረ ውድድር፤ ህገ ወጥ ንግድ፤ ኢ- ስነ ምግባራዊ እና ሙስና ተግባራት የፀዳ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት በዘርፉ ስር ሰባት ተቋማት ያሉ ሲሆን እነዚህም፡- በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፤ የኢትዩጵያ ምርት ገበያ፤ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስትቲትዩት፤ የኢትዮጵያ ተስማምነት ምዘና ኢንስትዩት፤ የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን ድርጅት፤ የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ስነ ልክ ኢንስትዩት ናቸው፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሥር በሚገኙ ተቋማት ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

1.3.2. ንዑስ አላማዎች፡-

የዚህ ጥናት ንዑስ አላማዎች በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት፥ 1) የአሠራር ስርዓት የስራ አፈፃፀምን መገምገም፤2) የሙስና ስጋትን ግምገማዊ ጥናት በማካሄደ መተንተን እና ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ ሃሳቦችን ማስቀመጥ ናቸው፡፡

1.4. የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ምንነትና ጠቀሜታው

ሙስና የሚለው ቃል የመጣው ከላቲን 'corrumpere' ሲሆን ትርጉሙም ህግና ተግባርን ማፍረስ፣ ህጋዊ አገዛዝን፣ የሞራል ደረጃን እና የግለሰብና የማህበረሰብን ስብዕናዎች በከፋ ሁኔታ ማበላሸት (Farida,

2006)። ሙስና በተለያዩ ተቋማትና ፀሃፊዎች ስለ ሙስና የተለያዩ ትርጉሞች ቢሰጡም በርካታ የጋራ ባህሪያትን የሚያመለክት ነው። በአለም ባንክ ትርጉም መሰረት ሙስና መንግስታዊ ሃላፊነትን ለግል ጥቅም ማዋል እንደሆነ ይገለፃል (Huther,2000)።

ግለሰቦች ወደ መንግስት ሃላፊነት በሚመጡበት ጊዜ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በህግና በአግባብ እንዲጠቀሙበት ቢጠበቅም ይህንን ሃላፊነት ለግል ጥቅም ማካበቻ የሚያውሉበት ሁኔታ ካለ ሙስና ተደርጎ ይወሰዳል። በተመሳሳይ መልኩ ሙስና የግል ጥቅምን ለማግኘት በሚል ሃላፊነትን ባግባቡ አለመጠቀም ወይንም ሃላፊነትን ተጠቅሞ ያልተገባ ነገር ማድረግን ይመለከታል። ሃላፊነትን ለግል ጥቅም ማዋል በሚለው እይታ ውስጥ በርካታ ተግባራት ሊዘረዘሩ ይችላሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 881/2015) 25 የሙስና ወንጀል ተግባራት በዝርዝር ቀርበዋል። የዚህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ጠቀሜታው፦ ይህንን ጥናት ስፖንሰር ያደረገው የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እስከሆነ ድረስ ለሙስና የተጋለጡ ዘርፎችን በመለየት ቀጣይ ዝርዝር የሙስና መከላከል ጥናቶችን ለማካሄድ ኮሚሽኑ በራሱ መንገድ ለፖሊሲ ግብአት ሊጠቀምበት ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ ለቀጣይ ከሙስና ጋር በተያያዘ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ አንድ ማጣቀሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ክፍል ሁለት፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የሙስና ስጋት የተዛማጅ ጹሁፎች ዳሰሳ

በአለም ላይ ከሙስና የፀዳ አንድም ሀገር የለም (ኡጋዝ፣ 2015)። ሙስና ለድህነት፣ ለግጭት እና ለአገር አለመረጋጋት አንዱ እና ዋንኛ መንስኤ ነው። ሙስና ተቋማት አገልግሎቶችን በብቃት የመስጠት እና የህግ የበላይነትን የማስጠበቅ አቅማቸውን በእጅጉ ያዳክማል፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚጎዳ እና የህብረተሰቡን ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መዋቅር የሚበላ ካንሰር ነው (ቤኖን 2009)። ሙስና ልክ እንደ ሽብርተኝነት ለብሔራዊ ደህንነት ስጋት ነው (ሚይንት፣2000)። በግምት ወደ አንድ ትሪሊየን ዶላር በዓለም ዙሪያ በሙስና በየዓመቱ ይባክናል (Stapenhurst et.al 2006) ።

2.1. በዘርፉ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

ሙስና የህግ የበላይነትን ያዳክማል፣ የህይወትን ጥራት ይሸረሽራል፣ ገበያን ያዛባል፣ የዜጎችን ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል (OECD 2018)። ጉቦ በዘርፉ በጣም የተስፋፋ ክስተት ነው። በመሆኑም ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ፣ ሞራላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስጋቶችን ያስከትላል፣ መልካም አስተዳደርን ያዳክማል፣ ልማትን ያደናቅፋል፣ ውድድርን ያዛባል፣ ፍትህን ይሸረሽራል፣ ሰብአዊ መብቶችን ያዳክማል እንዲሁም ድህነትን ለማስወገድ እንቅፋት ይሆናል። በተጨማሪም የንግድ ሥራ ወጪን ይጨምራል፣ በንግድ ግብይቶች ላይ እርግጠኛ ያልሆኑ ሁኔታዎችን ያስተዋውቃል፣ የሸቀጦችና የአገልግሎት ዋጋን

ይጨምራል፣ የምርት እና የአገልግሎት ጥራትን ይቀንሳል፣ ለህይወት እና ለንብረት መጥፋት ይዳርጋል፣ በተቋማት ላይ ዜጎች እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፣ ውጤታማ በሆነ የገበያዎች አሠራር ጣልቃ ይገባል፡፡

በታክስ አስተዳደር ላይ ሙስና የሚፈጸመው የታክስ ባለሥልጣኖችና ግብር ከፋዮች ከግብር ለማምለጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው (ካቤራ 2008)፡፡ ለምሳሌ በጋና የ2009 የአለም የሙስና ሪፖርት እንደሚያመለክተው አንዳንድ ከፍተኛ የታክስ ባለስልጣናት የታክስ ማጭበርበርን እየሸፈኑ እና ሚስጥራዊ ግንኙነቶችን ሲያደርጉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል (Transparency International 2009)፡፡ የግብር ባለሥልጣኖች ያለአግባብ የታክስ ነፃነቶችን ለማውጣት፣ ዝቅተኛ የግብር ተመኖችን ተግባራዊ ለማድረግ እና ግለሰቦችን ከግብር መዝገቦች በጉቦ ለመሰረዝ ስልጣናቸውን አላግባብ ይጠቀማሉ (McDevitt 2015)፡፡ እንደነዚህ ያሉት የጋራ እቅዶች የመንግስትን ካዝናን በመጉዳት ግብር ተቆጣጣሪዎችን እና ግብር ከፋዮችን ይጠቅማሉ(Antonakas, Giokas, and Konstantopoulos 2013)፡፡ በደቡብ አፍሪካ አንድ የጉምሩክ ባለስልጣን በሙስና ወንጀል ተከሶ በህገ ወጥ መንገድ ክፍያ በመቀበል ዝቅተኛ የግብር ተመኖችን አስከፍሏል (USTR 2014፣ዱት እና ትራካ፣ 2010)፡፡

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በሙስና እና በነጻ ገቢያ መካከል ያለው ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበት መግባባት ላይ አልተደረሰም። ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ለቢሮክራቶች የሚያጋጥሟቸው የማበረታቻ መዋቅሮች ብዙውን ጊዜ በገበያው የውድድር መዋቅር ላይ ተመስርተው ስለሚለያዩ በንድፈ ሀሳብ ምልክቱ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል። በተለይም አዴስ እና ዲ ቴላ (1999) ዝቅተኛ ፉክክር ባለባቸው አካባቢዎች ብዙ ትርፍ እንደሚገኝ እና በዚህም ሙሰኞችን ለመከታተል የበለጠ ማበረታቻ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ይህ ማለት ክትትልን መጨመር ዝቅተኛ ሙስናን ሊያስከትል ይችላል፣ ምንም እንኳን ተጨማሪ ትርፍ ለማምጣት የሚያገለግል ቢሆንም። ሌላው የንድፈ ሀሳቡ አሻሚነት ምክንያት የወጪ አወቃቀሮች እንደ ውድድር ደረጃዎች በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ ውድድር ከፍተኛ የሆኑ ቋሚ ወጪዎች ሲገደብ የአንድ ነባር ድርጅት ትርፍ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል ብለው ይከራከራሉ፡፡ ስለዚህ ገበያው ከፍተኛ ውድድር ባይኖረውም ሙስና ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል (Bliss and Di Tella (1997)፡፡

በተመረጡ 47 ሀገሮች የተካሄደው የምርምር ውጤት እንደሚያሳየው የምርት ገበያ ቁጥጥር ማድረግ ብዙም ጎልተው የማይታዩ ሙስናዎችን ለማየት እና ለመለየት ያስችላል (B.G. M, D.B.A 2018)፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ዓለም አቀፋዊ ንግድን በማቀላጠፍ እና እቃዎች በአስተማማኝ፣ ውጤታማ እና ፈጣን በሆነ መንገድ ድንበር እንደሚያቋርጡ በማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ለገቢ አሰባሰብ፣ እንዲሁም የዜጎችን ጥበቃና ደኅንነት ለማረጋገጥ ወሳኝ የሆኑ የተለያዩ ሕጎችንና ደንቦችን

የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ውስብስብ የጉምሩክ አሠራሮች፣ የትንበያ እና የተጠያቂነት ክፍተቶች፣ ዝቅተኛ የሞራል ደረጃ ወይም ዝቅተኛ ክፍያ የሚታሰበው እና በቂ ያልሆነ ቅጥር ትጋት ለጉምሩክ ባለሥልጣኖች አንዳንድ የሙስና አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል (OECD, 2017)፡፡ እንደዚህ አይነት የአደጋ መንስኤዎች፣ በድንበር ላይ ከተለጠፉት የጉምሩክ ባለስልጣኖች ጉልህ የሆነ የፍላጎት ስልጣን ጋር ተደምሮ ስልጣንን አላግባብ መጠቀምን ሊያስከትሉ ይችላሉ (U4, 2018)፡፡ በጉምሩክ መካከል ያለው የታማኝነት ክፍተት ህብረተሰቡን በህገወጥ ንግድ ለሚፈጠሩ አደጋዎች ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ በሙስና የተዘገበው ከፍተኛ መጠን ከሕገወጥ ድርጊቶች ጋር የተቆራኘ ነው፣ ለምሳሌ ለተፋጠነ ሂደት ጉቦ መስጠት፣ የግብር ስወራ፣ ማጭበርበር እና አስመሳይነት፣ አደንዛዥ እጾች እና ሌሎች በርካታ ህገወጥ ንግድ ዓይነቶችን በህገ ወጥ መንገድ ማዘዋወር (OECD፣ 2017)፡፡ የ2018 የ OECD ሪፖርት በደቡብ እና ምስራቅ አፍሪካ ህገ ወጥ የዱር እንስሳት ንግድ እና ሙስና ሪፖርት እንደሚያሳየው ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት ንግድ ወደ ውጭ መላክ እና ማጓጓዝ በጉምሩክ ባለስልጣናት መካከል ካለው የሙስና አውታሮች ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው (OECD, 2018)፡፡

2.2. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች

በዘርፉ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ሊዳርጉ ከሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች መካከል ስልጣንን አላግባብ መጠቀም እና ያልተገደበ ስልጣን ዋነኛው ሲሆን ግዴታን ችላ ማለት፣ አድሎአዊነት፣ አስተዳደራዊ ልዩነቶች እና ደንቦችን መጣስ፣ ተገቢ ያልሆነ ህግ፣ የመረጃ እና ምስጢራዊነት ጥሰቶች እና የጥቅም ግጭቶችን ያስከትላል፣ ፍትሃዊ ያልሆነ ውድድር፣ የተጋነኑ ወጪዎች እና የማህበረሰብ ተጽእኖ፣ ወደ ውጭ ለመላክ ወይም ለመሰብሰብ ወይም ለንግድ የተከለከሉ ዝርያዎች ፈቃድ ለማግኘት ጉቦ መስጠት፣ ከንግድ የተከለከሉ ዝርያዎችን ወደ ውጭ ለመላክ በተፈቀደው ላይ የውሸት መረጃን አውቆ ችላ ማለት ወይም ፈቃድ መስጠት፣ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ያልተለመዱ ነገሮችን የቅጣት ውሳኔ መስጠት፣ በማስረጃዎች ላይ የህግ ጥሰት መፈጸም፡፡

በመንግስት ግዥ እና በእርዳታ ላይ ያለውን ሙስና መቀነስ፣ የንግድ አካባቢን በዓለም አቀፍ ደረጃ ማሻሻል፣ ሙስናን ለመዋጋት ከሌሎች ሀገራት ጋር መስራት፣ በግዥ ማሻሻያ ላይ አረንጓዴ ወረቀቱን በማሳተም በመንግስት ዙሪያ ግልፅነትን እና ታማኝነትን የበለጠ ማጠናከር፣ በፀረ-ጉቦ ፖሊሲ ዙሪያ ስልጠና መስጠት፣ ለምሳሌ በስጦታ፣ በመስተንግዶ፣ በልገሳ እና መሰል ጥቅማጥቅሞች እና የማመቻቸት ክፍያዎች ዙሪያ መነጋገር እና ስልጠና መስጠት፣ መደበኛ የሆነ የአደጋ ግምገማ ማካሄድ፣ በኮንትራቶች ውስጥ የፀረ-ጉቦ ውሎችን ማካተት፣ ለድርጅቱ ጉቦ የመስጠት አደጋን ለመቀነስ የገንዘብ፣ የግዢ እና ሌሎች የንግድ ቁጥጥሮችን መተግበር፣ በጉቦ ዙሪያ ያሉ ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ የንግግር ዘዴን ማቅረብ፣ ጉቦ ተሰጥቷል የተባሉ ጉዳዮችን ለመመርመር እና የምርመራውን ውጤት ተከትሎ ተገቢውን እርምጃ

ለመውሰድ ሂደቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣ የድርጅቱን የፀረ-ጉቦ አካሄድ ትክክለኛ እና ዝርዝር መዝገቦችን መያዝ (U4፣ 2018)፣

በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት ክትትል እና ቀጣይነት ባለው መልኩ መከለሱን ማረጋገጥ። በኤርፖርቶች የማስመጣት እና የወጪ ንግድ ደንቦችን እና ሂደቶችን መገምገም፣ የማስመጣት እና የወጪ ፍቃድ አሰጣጥ ስርዓቶችን ማስማማት፣ የጉምሩክን ታማኝነት በሥነ ምግባር ደንብ ማሳደግ፣ ተቋማቱን ማጠናከር እና በወደብ ላይ የሚደረግ ፍተሻ ደህንነትን ማሻሻል። የሂሳብ ባለሙያዎች፣ መሐንዲሶች፣ ቀያሾች፣ የቀድሞ ፖሊስ አባላት እና ልምድ ያላቸው የመንግስት ሰራተኞችን የመሳሰሉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ችሎታ እና ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች መቅጠር፣ በሁሉም የደንበኛ ደረጃዎች ውስጥ ተሳትፎን ማሳደግ፣ የመከላከያ እርምጃዎችን ለማዳበር እና እንዴት እንደሚተገበሩ የሚከናወኑ ሥራዎችን መወሰን፣ እንደ የፍተሻ ማረጋገጫ ዝርዝሮች፣ ለአፈጻጸም ክትትል ዓላማ ምልክት ማድረጊያ ዘዴዎች፣ ለጨረታ ምዘና ላይ ምልክት ማድረጊያ ዘዴዎች ባሉ ይበልጥ የተዋቀሩ መንገዶች ላይ ማተኮር፣ ምልክቶቹን ብቻ ሳይሆን ዋና ዋናዎቹን እንደ ደካማ የአስተዳደር መዋቅር፣ ደካማ የሞራል፣ የመረጃ እጦት፣ የማይተገበሩ ህጎች እና በቂ ያልሆኑ ህጎችን በመመርመር ሙስናን ለመከላከል የበለጠ አለም አቀፍ አካሄድ መከተል እና የግልጽነት መርህን ማክበር ናቸው (Vaughan and Gebremichael 2011; Plummer et al. 2012)::::

ክፍል ሦስት፡ የዘርፉ የጥናት ሰነ ዘዴ

3.1. የጥናቱ ቦታ እና ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ በፌዴራል ደረጃ ባሉ የንግድና ቀጠናዎች ትስስር ዘርፍ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት ያለውን የሙስና ሥጋት ተጋላጭነት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ፡፡

3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል። የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች በመጠይቅ እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው። ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

መጠይቅ፡- የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው። በሌላ አገላለፅ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን

በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ስጋት ጥናት ነው፡፡

ሰነዶች፡- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከያ ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡፡

የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡- እንደሚታወቀው የሙስና ስጋቶች ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም የመለያየት ባሕሪ አላቸው፡፡ ስለሆነም ተቋም-ተኮር የሙስና ስጋት ልየታ ለማካሄድ በጥናቱ በተካተቱ ተቋማት ውስጥ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል፡፡

3.3. ጥናቱ የተከናወነበት ሂደት

ይህን ጥናት ለማከናወን በአማካሪዎች፣ በጥናት ቡድን መሪዎችና በመረጃ ሰብሳቢዎች አማካኝነት ሶስት ዋና ዋና ሂደቶችን የተከተለ ሲሆን፤ አንደኛው የጥናቱ መጠይቅ ዝግጅት ሲሆን መጠይቁን ለማዘጋጀት የተለያዩ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተሞክሮዎችን እና ተያያዥ ጽሁፎችን በመዳሰስ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል፡- የተዘጋጀውን መጠይቅ የሚመለከታቸው አካላት እንዲወያዩበት እና እንዲፀድቅ ተደርጓል፣ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለጥናት ቡድን መሪዎች የስልጠና ሞጁል በማዘጋጀት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በሁለተኛው ምዕራፍ የመረጃ መሰብሰብ ሂደት ሲሆን የመረጃው አሰባሰብ ሂደት በሁለት ዓይነት ዘዴ የተዘጋጀ ሲሆን 1ኛ) በሃርድ ኮፒ እና 2ኛ) በሶፍት ኮፒ የተቋማት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የመረጃዉን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ሁሉም መጠይቆች መረጃ ከተሞላባቸዉ በኋላ ከተሰበሰበው የሰነድ ማስረጃ ጋር እንዲረጋገጥ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም መረጃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት የመረካከቢያ ፎርም በማዘጋጀት ያልተሟሉ መረጃዎች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ተገቢ የሆኑ የስነ-ምግባር መርሆችን በመከተል፡- የግለሰቦችንም ሆነ የተቋምን መብት የማይጋፋ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንዲሁም የመረጃዉን ሚስጥራዊነት እንዲጠበቅ ተደርጓል፡፡ የሶስተኛው ሂደት የሪፖርት ዝግጅት ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ስለ ሪፖርት አጻጻፍ ለጥናት ቡድን መሪዎች እና አባላት ስልጠና ተሰጥቷል፣ በስልጠናው መሰረት የተዘጋጀውን ረቂቅ ሪፖርት ቀርቦ የሚመለከታቸው አካላት እነዲወያዩበት እና እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

3.4. የሙስና ስጋት ጥናት ስነ-ዘዴ

የተለያዩ የዓይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልቶች መካከል አንዱ የሆነውን ቲማቲክ (ጭብት ተኮር) የምርምር ዘዴ የተጠቀምን ሲሆን፤ ይህ የጥናት ዘዴ በመረጃ ውስጥ ፓተርንን (ርዕስን) የመለየት፣ የመተንተን እና

ሪፖርት የማድረግ ዘዴ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የመረጃውን መጠን የሚቀንስ ገላጭ የሆነ የትንተና ዘዴ ነው፡፡ ይህ አካሄድ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የዳሰሳ ጥናት መጠይቆች፣ የቡድን ውይይቶች እና በተለያዩ የጽሑፍ ስብስቦች ላይ ይተገበራል፡፡ ጭብጥ ትንተና ዘዴን በመጠቀም ተመራማሪው በጽሁፎቹ ውስጥ በተገለጹት ርእሶች እና ሃሳቦች ላይ ተደጋጋሚ ንድፎችን ወይም ጭብጦችን ለመለየት የመረጃ ስብስብ ያጠናል፡፡ የዓይነታዊ መረጃዎችን በመተንተን፣ የቲማቲክ (ጭብጥ ተኮር) ትንተና በፅንሰ-ሀሳቦች፣ አስተያየቶች እና ልምዶች ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ውስብስብ፣ ገላጭ እና በተለያዩ ፍልስፍናዊ እና ፅንሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች ላይ ሊያያዝ የሚችል የመረጃ አቀራረብን የሚጠይቅ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሙስና ስጋት ደረጃን ለመተንተን የአሀዛዊ መረጃ የትንተና ዘዴ የሆነውን የሙስና ስጋት ማትሪክስ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

3.5. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) እና (Corruption risk matrix) አሀዛዊ መረጃዎችን ለመተንተን ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (መጠይቅ፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎሊበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ዘዴን ተጠቅሟል፡፡

3.6. የጥናቱ ተግዳሮቶች

ጥናቱ የተለያዩ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል እነሱም፡- የተወሰኑ ተቋማት አዲስ በመሆናቸው ምክንያት የተሟላ መረጃ ለማግኘት መቸገር፣ በአንድ አንድ ተቋማት መረጃ የሚሰጡ ባለሙያዎች አለማግኘት፣ መረጃዎች ለማሳሰብ እና ለማደራጀት ጊዜ ማነስ እና የቀረቡ መረጃዎች የተሟላ አለመሆን፡፡

ክፍል አራት፡ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የሙስና ስጋት ትንተና በ11 ርዕሰ ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. ተቋማዊ አደረጃጀት

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ የስነምግባር መከታተያ አደረጃጀት በአመዛኙ በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የተሟላ መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር ከተደራጁት መከታተያ ክፍሎች አንዱ በጊዜያዊነት በውክልና የሚያሰራ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የስራ ክፍሉ ቢኖርም በተወሰኑት ላይ የተሟላ የሰው ኃይል የላቸውም፡፡ በአጠቃላይ በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ክፍል አደረጃጀት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለስራ ክፍሎች የተሟላ

ቁሳቁስና አመቺ ቢሮን በማሟላት ረገድ ከምርት ገቢያ በስተቀር ለስራ የሚያመች ቢሮ እንዲሁም በከፊል የተሟላ ቁሳቁስ እንዳላቸው በምልከታ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን በነዳጅና ኢነርጅ ባለስልጣን፣ተስማሚነት ምዘና ደርጅት ተቋማት ለጥቆማ አመቺ ያልሆነ ቢሮ መኖሩን የስራ ቁሳቁስ በማሟላት በኩልም ውስንነት ያለው መሆኑን በምልከታ ታይቷል፡፡ በዘርፉ ውስጥ የኢትዮጵያ አክሪዴሽን አገለግሎት ለክፍሉ የተሰጠ ቢሮም ሆነ ቁሳቁስ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ለመከታተያ ክፍሎች የሚካሄድ የበጀት ምደባን በሚመለከት አብዛኞቹ የዘርፉ ተቋማት ስር የተደራጁ የስነምግባር እና የፀረ ሙስና የስራ ክፍሎች ራሱን የቻለ መደበኛ በጀት የሌላቸው ሲሆን አብዛኞቹ ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ወይም ፕሮግራሞች ጋራ በጦል ከተመደበ በጀት ለተግባራት አፈጻጸም የወጪ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት የሚፈቀድበትና ተግባራዊ የሚደረግበት አሰራር መኖሩን ማየት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ለስራ ክፍሉ ራሱን የቻለ በጀት የሚመድብበት አሰራር መዘረጋቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የ2015 በጀት የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና እቅድ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት መኖሩን መረጃዎች ያሳዩ ሲሆን የኢትዮጵያ ምርት ገቢያ መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት ክፍሉ በቅርብ ጊዜ የተቋቋመ በመሆኑ የግማሽ አመት እቅድ ብቻ ያዘጋጀ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዘርፉ በአብዛኞቹ ተቋማት የሀብት ብክነትና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች መኖራቸውን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን በተስማሚነት ምዘና ድርጅት የተወሰኑ አደረጃጀቶች ብቻ መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ጥቆማ መቀበያ ስልቶች ለምሳሌ፡- ስልክ፣ ኢሜልና የሀሳብ መስጫ ሳጥን ስርዓት በአብዛኛው ተቋማት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በጥቂት የዘርፉ ተቋማት ግን የተወሰኑት ጥቆማ መቀበያ ስርዓቶች ብቻ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ሁኔታ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድረገጽ የሚጠቀሙ የተወሰኑ ተቋማት መኖራቸውን ማየት የተቻለ ሲሆን በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ምንም አይነት የጥቆማ ስርዓት የሌላቸው መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በዘርፉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በቅንጅት በመስራት ረገድ ውስንነቶች ያሉ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ አንድ ተቋም ከሰው ኃይል ጋር እንደሚሰራ በቃል ደረጃ ቢገለጽም ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ የኢትዮጵያ አክሪዴሽን አገልግሎት እና የኢትዮጵያ ምርት ገቢያ ምንም አይነት የቅንጅት ስራ እንደማይሰሩ ለማየት ተችሏል፡፡ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት የህግ ክፍል አስተያየት የሚሰጥበት በኢትዮጵያ ምርት ገቢያ ብቻ ሲሆን በሌሎች ተቋማት አስተያየት ስለመስጠቱ የሚገልጽ መረጃ የለም፡፡ በዘርፉ ያሉ ተቋማት በስራቸው ውስጥ ጣልቃ ገብነት ስለመኖሩ የቀረበ መረጃ የለም፡፡

ከተቋማዊ አደረጃጀት አኳያ በዘርፉ ስር በሚገኙ በአብዛኞቹ ተቋማት የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሉ ራሱን የቻለ የተመደበለት በጀት አለመኖሩ እና በበቂ የሰው ሃይል ባለመሟላቱ ስራውን በውክልና እንዲሰራ መደረጉ፣ የሚከናወኑ ለስነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ተግባር ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ አጠቃላይ የንግድ ስርዓቱ የሚመራበት በመሆኑ የሚካሄዱ ውሎች በህግ ክፍል አስተያየት የማይሰጥባቸው መሆኑ ማንኛውም ፍቃድ ወይም ማረጋገጫ የመስጠት ሃላፊነት ያለው ሰው ሆን ብሎ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው የተለያዩ ውሎችን ወይም ፍቃዶችን ሊያጸድቅ ይችላል፡፡ በመሆኑም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማጽደቅ የሙስና ወንጀል ስጋት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

በዘርፉ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን የአሰራር ስርአት ጥናት ከማካሄድ አንፃር የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በተለያዩ ርእሶች ላይ (በደረጃ እድገት አሰጣጥ እና በግዢ ክፍል) የአሰራር ስርዓት ጥናት ማካሄዱን እንዲሁም ጥናቱን ለማካሄድ መጠይቆችን ማስሞላቱን ከጥናቱ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን በአሰራር ስርዓት ጥናቶች መሰረት የማሻሻያ ሀሳብ ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ ቀሪዎቹ አምስት ተቋማት ግን ምንም አይነት የአሰራር ስርአት ጥናት አለማካሄዳቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የኢትዮጵያ ተስማሚነትና ምዘና ኤጀንሲ፣የኢትዮጵያ ምርት ገቢያ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በራሳቸው አቅም የደንበኞች እርካታ ያጠኑ መሆናቸውን ካቀረቡት ሰነድ የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪዎቹ ተቋማት ግን በገለልተኛ አካልም ሆነ በራሳቸው አቅም ምንም አይነት የደንበኞች እርካታ ጥናት አለማካሄዳቸውን መረጃዎቹ ያመላክታሉ፡፡

ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል ተቋማት የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) የማዘጋጀት እና የመተግበር ስራ አንዱ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር በዘርፉ ስር የሚገኙ አብዛኞቹ ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀታቸውን እና ለሰራተኞቻቸው ተደራሽ ማድረጋቸውን ከሰነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ አክሪዴሽን አገልግሎት ግን የተቋማቸውን የስራ መሪዎች እና የሰራተኞች የስነምግባር መመሪያ አለማዘጋጀታቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በተቋማት ትኩረት ከሚሰጥባቸው ተግባራት አንዱ የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት በሚደርሱ ጥቆማዎች መሰረት ቅድመ-መከላከል ስራዎችን መስራት ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ በዘርፉ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን በነዳጅ ስርጭት፤ በሰራተኞች ግዚያዊ ዝውውር እና በመኪና ጎማ እንዲሁም መለዋወጫ እቃዎች ግዢ ላይ የደረሳቸውን ጥቆማ ተቀብለው የፈቱ መሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን በአብዛኞቹ ተቋማት

በዚህ ዙሪያ የደረሳቸው ጥቆማ እና የሰሩት የቅድመ መከላል ስራዎች መኖራቸውን የሚያሳይ መረጃ እንዳላቀረቡ ከመረጃዎቹ መረዳት ተችሏል፡፡

በዘርፉ ወስጥ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ምርት ገቢያ ባለስልጣን በስነ- ምግባር ጉድለት ምክንያት በፈጻሚ አካላት ላይ የቀረቡ 18 ክሶች መኖራቸውን እና 6 ውሳኔ ያገኙ ሲሆን 12ቱ ወደ ፍርድ ቤት ማምራታቸውን የቀረቡ ሰነዶች ሲያመለክቱ ከስራ የማባረር፣ ከደረጃው ዝቅ የማድረግ እና የደሞዝ ቅጣት በተቋማት የተወሰዱ እርምጃዎች መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌሎች የዘርፉ ተቋማት ግን በስነ ምግባር ጉድለት የተከሰሱ አመራሮችም ሆነ ፈፃሚ አካላት ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በዘርፉ ስር ከሚገኙ ሰባት ተቋማት ውስጥ በሶስቱ ተቋማት በፍትሀብሔር እና በወንጀል ጉዳዮች 10 ክሶች የተመሰረቱ እና በይግባኝ ክርክር የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል በ6 (60%) በሚሆኑት መዛግብት የረታ ሲሆን በአንድ መዝገብ የተረታ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በቀሪዎቹ ተቋማት ላይ ግን ምንም አይነት የክስ ሂደቶች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ አለመገኘቱን ጥናቱ ያሳያል፡፡

በዘርፉ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ተሰማሚነትና ምዘና ድርጅት እና የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በርካታ ተገልጋዮች ያሏቸው ከመሆኑ አንፃር በርካታ ቅሬታዎችን ያስተናገዱ ሲሆን በተቋሞቹ ባለፉት ሁለት ዓመታት 45 ቅሬታዎች ቀርበው 33 ውሳኔ የተላለፈባቸው ሲሆን ቀሪዎቹ 8ቱ ግን በሂደት ላይ መሆናቸውን የቀረቡት ሰነዶች ያሳያሉ፡፡ በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን ሪፖርት እንደሌሎቹ ስራ ክፍሎች በሩብ ዓመት፣ በግማሽ አመት እና በስድስት ወር እንዲሁም በየዓመቱ የሚታይ ከመሆኑ ውጪ በተናጠል የክፍሉ ስራ በሃላፊዎች ስለመገምገሙ የቀረበ ሰነድ አለመኖሩን መረጃዎች ያሳያል፡፡ የጥቂት ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሳምንታዊ ሪፖርት ለአመራሩ የሚልኩ ቢሆንም ከአመራሮች የሚሰጥ ግብረመልስ ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡

ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አኳያ በዘርፉ ስር በሚገኙ አብዛኛው ተቋማት ሙስናንና ብልሹ አሰራር ለመከላከል የሚያስችሉ የአሰራር ጥናቶች በአብዛኛዎቹ ተቋማት የማይተገበር መሆኑ፣ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን ሪፖርት በተቋሙ የበላይ አመራሮች አለመገምገሙ እና ግብረ መልስ አለመስጠቱ እንዲሁም የተጠኑ ውስን ጥናቶች በተሰጠው ምክረ ሀሳብ መሰረት የማሻሻያ ስራ አለመደረጉ፡፡

4.3. የተቋማት ግልጽነት

ተቋማት ራሳቸውን ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ አላማቸውን ለማሳካትና አፈፃፀማቸውን ለማሳደግ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ግልፅነት ሙስናን ለማስወገድ ከሚያስችሉ መሰረታዊ

ተግባራት አንዱ ነው፡፡ ይህን ለማሳካትም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅና አሳታፊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ተቋማዊ ግልፅነት ማስፈን ጠቃሚ እና ወሳኝ መርህ ተደርጎ መወሰዱ ተገቢ ያደርገዋል፡፡ ተቋማዊ ግልፅነት ማለት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥን ያጠቃለለ ነው፡፡ ግልፅነት የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳ መልካም ውጤት ቢመዘገብም ሂደቱ የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡

በዘርፉ ተቋማዊ ግልፅነት ለማስፈን እንዲያግዝ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ከመረጃ ስብሰባው ሂደትና መስክ ምልከታው መረዳት ተችሏል፡፡ ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጠናከር ያቀዷቸው ዕቅዶች እንዲሳኩ ለማድረግ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ካለፈው ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በመነሳት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በማዘጋጀት፣ በዕቅዱ ላይ ግልጽ ውይይቶችን በማድረግና የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ወደ ተግባር ስለመግባታቸው ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር እንደተገባ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

አብዛኛዎቹ ተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በየተቋማቱ ተደራሽ እንደሚያደርጉ ነገር ግን የኢትዮጵያ ተስማሚነትና ምዘና ድርጅት መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በየተቋማቱ ተደራሽ አንደማይደረግ በመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚካሄድ ተሳትፎ እና ውጤትን ተደራሽ በሚመለከት ሁሉም ተቋማት በማኔጅመንት ደረጃ የሚደረግ ውይይት ቃለ-ጉባኤ ለማየት እንደተሞከረው የተለያዩ ውሳኔዎች የሚመለከታቸውን የስራ ክፍሎች የሚያሳትፉ ሲሆን በስራ ሂደትና አጠቃላይ በሰራተኞች ደረጃ ግን የተለመደ አለመሆኑን ከመረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ያሉ አብዛኛዎቹ ተቋማት ውሳኔዎች ለህዝብ እና ለሚመለከታቸው አካላት በመገናኛ ብዙኃን እና በማህበራዊ ሚዲያ በተከታታይ ተደራሽ እንደሚደረግ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን በኢትዮጵያ ተስማነትና ምዘና ድርጅት ግን የሚወሰኑ ውሳኔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው መረጃ የለም፡፡

በዘርፉ ያሉ አብዛኛዎቹ ተቋማት የግዥ ጨረታ ማስታወቂያዎች በአዲስ ዘመን ጋዜጣና ዌብሳይት በይፋ ለተገልጋዮች ማሰራጨትን በተመለከተ በአብዛኛው ተቋማት ተግባራዊ እንደሚደረግ ለማየት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት የተገልጋይና ባለድርሻ አካላት በቀላሉ የሚፈልጓቸውን መረጃዎች በየተቋማቱ የሚገኙ መሆኑና ተደራሽ እንደሚሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር አወንታዊ ስራ እየተሰራ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

4.4. አዋጅ፣ ድንብና መመሪያ

ሙስናን መዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፍን ባሻገር ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፋፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በጥናት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመነሳት አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ በተቋማቱ እየተሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ደረጃዎች አዘገጃጀትና ማስተግበሪያ ረቂቅ አዋጅ፣ የህጋዊ ስነ-ልክ ረቂቅ አዋጅ፣ የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ፣ የእቃ ማካማቻ ደረስኝ ረቂቅ ደንብ፣ የኢትዮጵያ አክርድቴሽን ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ፣ የንግድ ምዝገባ ፍቃድና ድህረ ፈቃድ ኢንስፒክሽን ማሻሻያ መመሪያ እና የኢትዮጵያ ንግድ ፍቃድ መስጫ መደቦች ማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ ሁሉም ተቋማት በሚባል ደረጃ የሥነ-ምግባር ደንቦችና ሙስና መከላከል የሚያስችል መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ እያደረጉ መሆናቸውን ከቀረቡ ሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከዚሁ በተጓዳኝ ህጎችን በፍትህ ሚኒስቴር የማስመዝገብ አሰራር ያለ መሆኑን ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ለአብነትም የንግድ ፍቃድና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ማሻሻያ መመሪያ 935/2015 ጸድቆና በፍትህ ሚኒስቴር መመዝገቡን መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎቹ ተቋማት የውስጥ መመሪያዎችን በፍትህ ሚኒስቴር የማቅረብና የማፀደቅ ልምድ ውስንነት ያለ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ውጪ የሚዘጋጁ ደንቦችና አዋጆች ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ ለፍትህ ሚኒስቴር፣ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር ወ.ዘ.ተ በመላክ እና ክትትል በማድረግ ረገድ አወንታዊ እርምጃዎች መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዘርፉ ከ50 በላይ ደንቦችና መመሪያዎች የወጡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 33ቱ የተሻሻሉ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ለተገልጋዮች/ለደንበኞች በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ ረገድ በተለይም በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችና በበየነ መረብ (website) ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን የተቋማቱ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አተገባበር ዙሪያ በንግድና ቀጠናዊ እና የኢትዮጵያ ተስማነትና ምዘና ለአመራሮች እና ሰራተኞች ሥልጠና ስለመስጠታቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአንጻሩ በአምስት ተቋማት በወጡ ህጎችና መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ የዜጎች ቻርተርን

በተመለከተ ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ያዘጋጁ ሲሆን ተደራሽ በማድረግ በኩል አብዛኞቹ ተቋማት መልካም ጅምር ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተደራሽ አልተደረገም፡፡ በአጠቃላይ ከአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አንፃር በዘርፉ የታዩ ክፍተቶች፡- የሚወጡ መመሪያዎች በፍትህ ሚኒስቴር የማቅረብና የማፀደቅ ልምድ አነስተኛ መሆኑ እና የሚወጡ ህጎች ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ በመፍጠር በኩል በተሟላ ሁኔታ የማይሰራ መሆኑን ይህም የመንግሥት አሠራሮች አስገዳጅነት ባላቸው መመሪያዎች እንዳይመሩ እና ሠራተኞችም ከግንዛቤ ክፍተት ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

4.5. የንብረት አስተዳደር

በዘርፉ በአምስቱ ተቋማት የንብረት አስተዳደር እና መቆጣጠር አሰራር ስለመኖሩ ከተሰበሰቡ ሰነዶች ማረጋገጥ የተቻለ ቢሆንም ንግድና ቀጠናዊ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ተቋማት ግን የንብረት ማስተዳደርና መቆጣጠሪያ ስርዕት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ ሆኖም ተግባራዊ የተደረጉ የንብረት አስተዳደርና መቆጣጠሪያ ስርዓት መዘርጋቱ በበጎ መልኩ የሚታይ ቢሆንም ሁሉም ተቋም በሚባል ደረጃ ከቢን ካርድ ውጭ ሌላ አማራጭ ስርዓት እየተጠቀሙ እንዳልሆነ ከሰነዶች ማየት ተችሏል፡፡ የንብረት ቆጠራን በተመለከተ ሶስት ተቋማት በየአመቱ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መረጃ ያልተገኘ ሲሆን አራቱ ተቋማት ግን በየአመቱ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ማድረጋቸውን የሰነድ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ተቋማት የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ በዘርፉ በስድስት ተቋማት በ2013 እና 2014 የተወገዱ ንብረቶች መኖራቸውን በመረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ ስነልክ ኢንስቲትዩት ምንም አይነት ንብረት ቆጠራ መከናወኑን የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር ቀርቦ በባለሙያ ተገምግሞ መወገድ እንዳለበት በተደነገገው መሰረት በዘርፉ በሚገኙ ስድስት ተቋማት እንዲወገዱ የተለዩ ንብረቶች ዝርዝር በባለሙያዎች ተገምግመው በስጦታ እንዲሁም በግልፅ ጨረታ እንዲወገዱ የተደረገ መሆኑን ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የአንድ ተቋም የንብረት ማስወገድ ተግባር በሂደት ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በንብረት አስተዳደር የታዩ ክፍተት አንዱ በሁሉም ተቋማት የካይዘን አሰራር ስርዓት በተሟላ ሁኔታ የማይከናወን መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሆነም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የዕቃና የአገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችን ለማሟላት የግዥ ስርዓትን የተከተለ ስልታዊ የሆነ አካሄድ መከተል ይጠይቃል፡፡ የዘርፉን የግዥ አፈፃፀም ሂደት በሚመለከት በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና በስተቀር ሁሉም ተቋማት የግዥ እቅድ ያላቸው ሲሆን በግዥ እቅዳቸው ላይ ግምገማ እንደሚያደርጉ የግምገማ ሪፖርት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት የዘርፉ ተቋማት የግዥ ፍላጎታቸውን መሰረት በማድረግ በርካታ ግዥዎችን ያከናወኑ ሲሆን ከኢትዮጵያ ተስማነትና ምዘና በስተቀር ሁሉም ተቋማት የግዥ አፈፃፀም ግምገማ እንደሚያደርጉ ከሰነድ ማስረጃዎች ማየት ተችሏል፡፡

የዘርፉን የ2014 በጀት ዓመት የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎችን በሚመለከት አራት ተቋማት በእቅድ፣ አምስት ተቋማት በፐርፎረማ፣ አምስት ተቋማት በውስን ጨረታ እና ሁለት ተቋማት በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ ግዥ ያከናዎኑ መሆናቸውን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቅሬታ የቀረበበትም ሆነ የተሰረዘ ግዥ ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ የግዥ ሂደትን ለማከናወን አምስት የዘርፉ ተቋማት ስቶክ ላይ ያላቸውን እቃ ተመርኩዘው ግዥ እንደሚፈፅሙ ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ሌሎች ሁለት ተቋማት ስቶክ ላይ ተመስርተው ግዢ ስለመፈፀማቸው የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡

ግዥ ከመፈፀሙ በፊት የገበያ ጥናት መከናዎኑን በሚመለከት ሦሥት ተቋማት ቅድመ ገበያ ጥናት አካሄደው ግዥ መፈፀማቸውን ከተሰበሰበው የገበያ ጥናት ሪፖርት ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ሌሎች አራት ተቋማት የቅድመ ገቢያ ጥናት አለማከናወናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዲጂታል የታገዘ የግዥ አሰራር ሥርዓትን ከመተግበር አንፃር አራት ተቋማት በዲጂታል ስርዓት እንደሚተገበሩ ከሰነድ ማስረጃና ከሲስተም ምልከታ የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪው የኢትዮጵያ ነደጅና ኢነርጅ ባለስልጣን በዲጂታል የታገዘ አሰራር ሰርዓት አለመኖሩን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ከግዥ አስተዳደር አንፃር በዘርፉ ስር የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የቅደመ ገበያ ጥናት የማይከናወን መሆኑ በማንኛውም ዓይነት የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ በተጋነነ ዋጋ ግዥ ሊከናወን ይችላል፡፡

4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር

በዘርፉ በሁሉም ተቋማት የሰራተኛ አስተዳደር የስራ ክፍል የተለያዩ ኮሚቴዎች፡- የቅጥር፣ የዝውውር እና የዲሲፒሊን ኮሚቴዎች ተቋቁመው በተግባር ላይ መሆናቸውን ከቀረቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም በዘርፉ ሥር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ላይ የቅጥር ማስታወቂያዎች በጋዜጣና በተለያዩ ዘዴዎች ለስራ ፈላጊዎች ተደራሽ እንደሚደረግ ከሰነድ መረጃዎች ለማየት ተችሏል::

በዘርፉ ስር በሚገኝ በደረጃዎች ኤጀንሲ ሁለት ቅሬታ ቀርበው ሁለቱም መፍትሄ ያገኙ ሲሆን በተቀሩት ተቋማት ግን ቅሬታ ስለመቅረቡ መረጃ የለም፡፡ ሀሰተኛ የትምህርትና ሥራ ልምድ መረጃ ማጣራትን በተመለከተ በአብዛኛው ተቋማት ላይ መረጃውን ስለማጣራታቸው የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ ሆኖም በሶስት ተቋማት ላይ በጅምር ደረጃ መረጃዎቹን ለማጣራት እየተሰራ መሆኑ መረጃው ያሳያል፡፡

የስራ አመራር ምደባን በተመለከተ በተለይም የዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች ቅጥር/ምደባ በሁሉም በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት በውድድር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከወጡ ማስታወቂያዎችና ቃለ-ጉባኤዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአንድ ተቋም የሰው ሀብት መረጃ ስርዓት በዘመናዊ መረጃ የታገዘ አሰራር እንደሚከተል በምልከታ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን በሌሎች የዘርፉ ተቋማት ግን ዘመናዊ የሰው ሀብት መረጃ ስርዓት ስለመዘርጋታቸው የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡

የብቃት ማሻሻያ ስልጠናዎችን በተመለከተ በአራት ተቋማት ላይ በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ላይ ለአመራሮችና ሰራተኞች የሙያ ብቃት ማጎልበቻ ስልጠና ስለመሰጠቱ ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም የሥነ ምግባር ማሻሻያ ላይ የተሰጡ ስልጠናዎች በቂ አለመሆኑን ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡ ሶስት ተቋማት የብቃት እና የሥነምግባር ማሻሻያ ስልጠና ስለመስጠታቸው የሚያመለክት መረጃ የለም፡፡

ከሰው ሀብት አስተዳደር አኳያ በዘርፉ ባሉ አብዛኛው ተቋማት የሰው ሀብት የስራ ክፍል በዘመናዊ የመረጃ አሰራር ስርዓት የታገዘ አለመሆኑ እንዲሁም የሀሰተኛ የትምህርትና የሥራ ልምድ መረጃን የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ማንኛውም ሰው የራሱንም ሆነ የሌላውን መብትና ጥቅም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ስለሆነም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሃሰት መለወጥ ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል ስጋት ሊያጋልጥ የሚችል መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል፡፡

4.8 የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ

በዘርፉ ካሉት ተቋማት ውስጥ ሁሉም የሀብት ምዝገባ ስራ የሚያከናውኑ እና የሚከታተሉ መሆናቸውን ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም ከዘርፉ ካሉት ተቋማት ውስጥ ያስመዘገበ እና ያላስመዘገበ መረጃ በትክክል ለይተው ያቀረቡ ወይም ያደራጁ ሦስት ተቋማት ብቻ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በዘርፉ ሀብት ማስመዝገብ ካለባቸው 1,671 አስመዝጋቢዎች 953 ሠራተኞች እና 14 አመራሮች ሀብታቸውን ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ ከዘርፉ ውስጥ የምርት ገበያ ባለስልጣን ብቻ ገና ጅምር ስራ ላይ ያለ በመሆኑ የሀብት ምዝገባ ስራው

በሂደት ላይ ሲገኝ የሌሎች ተቋማት ግን የተሻለ የሀብት ምዝገባ ስራ እንደሚያከናውኑ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዘርፉ የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት ሃብት ያስመዘገቡ እና ያላስመዘገቡ ሰራተኞች እና ሃላፊዎችን መረጃ በትክክል ለይተው ማቅረብ አልቻሉም፡፡ በዚህም ምክንያት በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት ሃላፊዎች እና ሰራተኞች በህገ ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው ሊያውሉት ይችላሉ፡፡

4.9. የፕሮጀክት አስተዳደር

በዘርፉ ያሉ ተቋማትን ፕሮጀክቶች ሁኔታ አስመልክቶ ከተሰበሰበ የሀርድ ኮፒና የሶፍት ኮፒ መረጃዎች ማረጋገጥ እንደተቻለው ምርት ገበያ ባለስልጣን ተቋም ፕሮጀክት ያለው ሲሆን የፕሮጀክቶቹ አይነት፣ የተመደበላቸው በጀት፣ ያሉበት ደረጃና የሚከናወኑበት ቦታና ሳይት በአፈጻጸም ሪፖርቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ፕሮጀክቶቹ ከሙስናና ብልሹ አሠራር ተጠብቀው እንዲከናወኑ በማስቻል ዙሪያ ተቋሙ እያደረገ ስላለው ክትትልና የቁጥጥር ስርአትን አስመልክቶ ምን እንደሚመስል የሚያረጋግጥ የሠነድ ማስረጃ የለም፡፡

4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ለማረም የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀታቸውን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ጥሩ ቢሆንም ከሁለት ተቋማት በስተቀር የውጭ ኦዲት ሪፖርት የሌለ መሆኑን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ በተሰበሰበ መረጃ መሰረት በትክክል ያልተወራረዱ፣ ያላግባብ የተወሰዱ እንዲሁም ያላግባብ ተወስደው ተመላሽ የተደረጉ በሚል ለይቶ ማስቀመጥ ባይቻልም ከሁለት ተቋማት ግን በውስጥ ኦዲተር ያልተወራረደ ተብሎ የተገለጸው 30898 ብር፤ በውጭ ኦዲተር ደግሞ የተገለጸው 88079 ብር መሆኑ ማየት የተቻለ ሲሆን 66000 ብር ተመላሽ የተደረገ መሆኑን ከኦዲት ሪፖርቶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የተወሰኑ ተቋማት ብቻ የተቋሙ አመራር የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ ማድረጋቸው ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ሁሉም ተቋማት የኦዲት ሪፖርቶችን ተመስርተው ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው የሚያመላክት መረጃ የለም፡፡ እንዲሁም የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ተደራሽ ስለመደረጋቸው በቂ መረጃ የለም፡፡ በዘርፉ በተጠና ጥናት ውጤት መሰረት የኦዲት ሪፖርቶችን ተመስርተው ማሻሻያዎች አለማድረግ ከፍተኛ የሙስና ሥጋት፤ በውጭ አካል ኦዲት አለማስደረግ መከከለኛ ሥጋት እንዲሁም የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ተደራሽነት አለማድረግ ደግሞ ዝቅተኛ ሥጋት መሆኑን በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

ስለሆነም በዘርፉ የሚገኙት አብዛኛው ተቋማት በውጭ አካል ኦዲት አለመደረግ፣ የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶችን ተመስርተው ማሻሻያዎችን አለማድረግ እና የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶችን ለሚመለከተው አካል ተደራሽ አለማድረግ የመመሪያ ጥሰትን፣ የቁጥጥር ሥርዓት መላላትን፣ የሚሰጡ አስተያየቶች ተግባራዊ አለማድረግን፣ የገንዘብ ብክነትን እንዲሁም ለብልሹ አሠራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

4.11. የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የንግድ እና ቀጥናዊ ትስስር ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት የስራ ክፍሎችና ሂደቶች መደበኛ ስራቸውን ሲያከናዉኑ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን የመለየት፣ የመከሰት ዕድላቸውን እና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችለውን ተጽዕኖ በደረጃ (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ) በማለት በማስቀመጥ በመጨረሻም የሙስና ስጋት ትንተና ተካሄዷል፡፡

የስራ ክፍሎች የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መካከለኛና ከባድ በመባል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው ሙስና በስራ ክፍሎች የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የነዳጅ ሎጂስቲክ ክትትልና ቁጥጥር፣የነዳጅና ትራንስፖርት ክትትልና ቁጥጥር፣ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ገባያ ጥናትና ምርመር፣የነዳጅ ተቋማት ደረጃ ማስጠበቅ አሰራር፣የኤሌክትሪክ እንስታሌሽን ፍቃድ አሰጣጥ፣ ገቢ እና ወጪ እቃዎች ጥራት ማረጋገጥ፣ የወጭ ንግድ ግብይት፣ የሀገር ውስጥ ንግድ ስርአት፣የግዥና ንብረት አስተዳደር፣ትሬድ ኦፕሬሽን፣ የቡና እና የቅባት ጥራት ክፍል፣ የስራ ክፍሎች ከባድ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው ክፍሎች ሲሆኑ የንግድና የምዝገባ ፍቃድ፣ ማከማቻ መጋዝን፣ ፕሮጀክት ክፍል እና ICT የስራ ክፍሎች መጠነኛ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው የስራ ክፍሎችና ሂደቶች መሆናቸውን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝር የመከሰትና የተጽዕኖ ደረጃውን በአባሪ ሀ ላይ ይመልከቱ፡፡

ክፍል አምስት፡ የመፍትሄ ሀሳቦች

- በዘርፉ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ስራውን ነፃና ገለልተኛ ሆኖ መስራት እንዲችል ራሱን የቻለ የበጀት ምደባ ቢኖረውና ክፍሉም ቋሚ በሆኑ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲሰራ ቢደረግ፣
- ተቋማቱ በተሟላና ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ የጥቆማ መስጫ ስርዓት እና አማራጮች እንዲዘረጋ ቢደረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት በተመረጡ ርእሰ ጉዳዮችን የአሰራር ስርዓት ጥናት እንዲያካሂዱ የሚያስችል አሰራር ቢዘረጋ ፤
- የተጠኑ ጥናቶች በቀረቡ ምክረ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ ስለመሆናቸው መረጃዎችን በማሰባሰብ ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ ቢቻል፤

- በዘርፉ የሚወጡ መመሪያዎችን በፍትህ ሚኒስቴር አሰተያየት እንዲሰጥባቸው እና እንዲፀድቁ የማድረግ ልምድ ቢጠናከር ፤
- በሚወጡ ህጎች ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጠል ቢደረግ ፤
- የካይዘን አሰራር ተግባራዊ ባልተደረገባቸው የዘርፉ ተቋማት ተግባራዊ ቢደረግ ፤
- ግልፅ የሆነ የግዥ አሰራር ስርዓት የሚጠናከርበት ሁኔታ ቢመቻች፤
- የቅደመ ገበያ ጥናት በሁሉም ተቋማት ተገባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ቢደረግ፤
- ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ መረጃ የማጠራት ስራዎች በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ማከናወን ቢቻል፤
- የስነ ምግባር ማሻሻያ ስልጠና በሁሉም የዘርፉ ተቋማት እንዲሰጥ ቢደረግ ፤
- የዘርፉ ተቋማት የኦዲት ሪፖርቶችን ተመስርተው ማሻሻያዎች እንዲያደርጉ ቢደረግ፣
- ዘርፉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶችን በተገቢው የመገናኛ አውታር ተደራሽ ማድረግ ቢችል።

ማጣቀሻ ጽሁፎች

1. Antonakas, N., Giokas, A., and Konstantopoulos, N. 2013. Corruption in Tax Administration: Interviews with Experts.
2. Ades, A., and R. Di Tella. "Rents, Competition, and Corruption." *American Economic Review*, **89**(4), 1999, 982– 93.
3. Bliss, C., and R. Di Tella. "Does Competition Kill Corruption?" *Journal of Political Economy*, **105**(5), 1997, 1001– 23.
4. Bahaudin G. Mujtaba, D.B.A፣ (2018). An Analysis of the Relationship between Regulatory Control and Corruption based on Product and Market Regulation and Corruption Perceptions Indices፣ Nova Southeastern University, USA፣
5. Benon, C. B. (2009). Determinants of Public Procurement Corruption: A Study on Uganda. (Accessed in January 2012).
6. Farida, M., & Ahmadi-Esfahani, F. (2006), Corruption and Economic Development: A critical review of literature, AARES 50th.
7. Manchin, R. (2000). An Assessment of corruption: Discovering a hidden society phenomenon, ed.R. Manchin, Istanbul, Hungarian Gallup Institute
8. Plummer, J. at al. 2012. Diagnosing Corruption in Ethiopia.
9. Stapenhurst, R., Johnston, N., & Pelizzo, R. (2006).The Role of Parliament in Curbing Corruption. The World Bank: Washington, D C.
10. Kabera, C. 2008. Effectiveness of Rwandan Law of Tax Administration in Addressing Tax Offences.
11. Transparency International 2009. Global Corruption Report: Corruption in the Private Sector.
12. McDevitt, A. 2015. Combatting Corruption in Tax and Customs Administration in Asia Pacific.
13. Ugaz, Jose (2015). Not one single country, anywhere in the world, is corruption free. In Corruption Perceptions Index 2015. Transparency International. Retrieved on February 10, 2017 from: www.transparency.org/cpi
14. Huther, J (2000). Anti-corruption Policies and Programs: A Framework for Evaluation, World Bank Working Paper, Series No. 2000, Washington D.C.
15. United States Trade Representative. 2014. Foreign Trade Barriers.
16. Dutt, P. and Traca, D. (2010), "Corruption and bilateral trade flows: extortion or evasion?", Review of Economics and Statistics, Vol. 92 No. 4, pp. 843-860.
17. Vaughan, S. and Gebremichael, M. 2011. Rethinking Business and Politics in Ethiopia: The Role of EFFORT, the Endowment Fund for the Rehabilitation of Tigray
18. The World Bank. 2014. Project Appraisal Document on a Proposed Credit in the Amount of SDR114 Million (US$176 Million Equivalent) and a Proposed SCF-SREP Grant in the Amount of US$24.5 Million to the Federal Democratic Republic of Ethiopia for a Geothermal Sector Development Project (GSDP).
19. U4 (2018), "Combatting corruption in tax and customs administration in AsiaPacific",
20. OECD/ADB (2018), *Government at a Glance: Southeast Asia 2018*, OECD Publishing, Paris, http://dx.doi.org/doi.org/10.1787/888933840266.

አባሪ ሀ፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስ ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ የስራ ክፍሎች እና ሂደቶች	የመከሰት እድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተፅኖ	የሙስና ስጋት	የስጋት መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
1.	የነዳጅ ሎጂስቲክ ክትትልና ቁጥጥር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የሰራተኛ እና ደንበኛ ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት	የቁጥጥር ስርዓት ማዳበር
2.	የነዳጅና ትራንስፖርት ክትትልና ቁጥጥር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የሠራተኞች ሥነስርአት መጉደል	የቁጥጥር ስርዓት ማዳበር
3.	ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ገባያ ጥናትና ምርመር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	እኩል ምደባ አለመኖር	ሲስተሙን ማጠናከር
4.	የነዳጅ ተቋማት ደረጃ ማስጠበቅ አሰራር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	በዘመድና በትውውቅ መስራት	የቁጥጥር ስርዓት ማዳበር
5.	የኤሌክትሪክ እንስታሌሽን ፍቃድ አሰጣጥ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ባለሀብትና ባለሙያ ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት	ጠንካራ የቁጥትር ስርዓትና ግንዛቤ ማሳደግ
6.	የንግድና የምዘገባ ፍቃድ	መካከለኛ	መካከለኛ	መጠነኛ	በጥቅም ትስስር ተገቢ ላልሆነ አካል ፍቃድ መስጠት	ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት
7.	ገቢ እና ወጪ እቃዎች ጥራት ማረጋገጥ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የሸቀጥና ነዳጅ ስርጭት መዛባት	በኮድ መስራት
8.	የወጭ ንግድ ግብይት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ውጭ ንግድ ስርአት መዛባት	አሰራሮችን ማሻሻል
9.	የሀገር ውስጥ ንግድ ስርአት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የነዳጅ እና ሸቀጦች ስርጭት መዛባት	አሰራሮችን ማሻሻል
10.	የግዥና ንብረት አስተዳደር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የገዥ ሂደቱ በተደጋጋሚ ከአንድ ቦታ መሆን	ሲስተሙን ማጠናከር
11.	ትሬድ ኦፕሬሽን	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ደንበኛ እና የሰራተኛ ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት	ሲስተሞን ማጠናከር
12.	ማከማቻ መጋዝን	መካከለኛ	መካከለኛ	መጠነኛ	ደንበኛ እና የሰራተኛ ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት	ቴክኖሎጂ መጠቀም
13.	የቡና እና የቅባት ጥራት ክፍል	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ደንበኛ እና የሰራተኛ ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት	ቴክኖሎጂ መጠቀም
14.	ፕሮጀክት ክፍል	መካከለኛ	መካከለኛ	መጠነኛ	ቶሎ አለመጠቀም	ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ
15.	ICT ክፍል	መካከለኛ	መካከለኛ	መጠነኛ	ሲስተሞ ላይ ቀድሞ መረጃ የማግኘት	ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ